Ethiopiawinet Radio

www. Ethiopiawinet.net

## ኃይሉ ሻውል በምርጫው ስለመወዳደራቸው አልወሰኑም

የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) ሊቀመንበር ኢንጅነር ኃይሉ ሻውል በቀጣዩ አገራዊ ምርጫ ስለመወዳደራቸውና አለመወዳዳራቸው እስከ አሁን ድረስ ያልወሰኑ መሆኑን ለሪፖርተር ጋዜጣ ገለጹ፡፡

"ልወዳደር ወይስ አልወዳደር?" የሚለውን ጉዳይ እያሰቡበት መሆኑን በሌላ በኩል ደግሞ የእርሳቸውን ኃላፊነት ሌላ ሰው ሊተካ በሚችልበት ጉዳይ ላይ ከፓርቲያቸው ጋር እየተነጋገሩበት መሆኑን የጠቆሙት ኢንጅነር ኃይሉ፣ የሚመሩት ፓርቲ የግድ መወዳደር እንዳለባቸው ከወሰነ ግን ተወልደው ባደጉበትና በሰሩበት በአዲስ አበባ እንደሚወዳደሩ ገልጸዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት እድሜያቸው 74 ዓመት መድረሱንና በዘንድሮው ምርጫ ከተወዳደሩ ደግሞ እስከ 79 ዓመታቸው ድረስ በፓርቲው ውስጥ ሊቆዩ እንደሚችሉ የገለጹት የመኢአድ ሊቀመንበር፣ የእድሜያቸውን መግፋት ትኩረት ውስጥ በማስገባት በአሁኑ ሰዓት እረፍት መውሰድ ስለሚፈልጉ በምርጫው ባይወዳደሩ እንደሚመርጡ ተናግረዋል፡፡

ከእርሳቸው ይልቅ ሌሎች የፓርቲው አመራር አባላት ለምርጫ የሚቀርቡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት እየመከሩ መሆናቸውን የጠቆሙት ኢንጅነር ኃይሉ፣ የእርሳቸው በምርጫው መሳተፍ ያን ያህል ጠቃሚነው ብለው እንደማያስቡ ገልጸዋል፡፡

ኢንጅነር ኃይሉ እንዳሉት፣ መኢአድ በሌሎች ክልሎች የሚወዳደሩ እጩዎችን እያቀረበ ቢሆንም፣ የአዲስ አበባ ተመራጮችን የማስመዝገቡ ጉዳይ ግን ማን የት መወዳደር አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ ተነጋግሮ የአንዳንድ ተመራጮችን መወዳደሪያ መለወጥ ስለሚያስፈልግ የጥቂት ተመራጮች ምዝገባ ዘግይቷል፡፡ የእርሳቸውና የሌሎች ቁልፍ ሰዎች መወዳደሪያ ቦታ ያልታወቀውም ከዚህ ጋር በተያያዘ መሆኑን አክለው ገልጸዋል፡፡

ኢንጅነር ኃይሉ እንዳሉት በዘንድሮው ምርጫ መኢአድ በትግራይ 50 በመቶ፣ በኦሮሚያ 30 በመቶ፣ በደቡብና በአማራ ክልል በሁሉም የመወዳደሪያ ጣቢያዎች እጩዎችን የሚያቀርብ ሲሆን፣ ተመራጮችን የሚያስመዘግቡ ቡድኖች ወደየክልሉ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ በዚህም መሠረት ሦስት ቡድን ወደ ደቡብ ክልል፣ ሁለት ቡድን ወደ ሰሜን፣ አንድ ቡድን ወደ ምሥራቅ እና ሁለት ቡድን ወደ ምዕራብ ተጉዟል፡፡